# ኃይለማርያም ደሳለኝን ለመበቀል ጥረት እየተደረገ ነው

ከደብተራው የዜና ምንጮች

ኃይለማርያም ደሳለኝ፣ የወያኔ ባለሥልጣናት ባላቸው የርስበርስ ሽኩቻ፣ በአንዱ ወገን አይዞህ ተብሎ፣ የአገዛዙን ሙሰኝነት እና አፋኝነት በስብሰባቸው ላይ ከተናገረና ከዚህም ውስጥ የተወሰነው ተቀነጫጭቦ በሚቆጣጠሩት የህዝብ መገናኛ ከቀረበ በሁዋላ፣ ለዚህ ድርጊቱ እርምጃ ካልተወሰደበት የሚሉ የወያኔ አመራሮች ግፊት እያደረጉ መሆኑን ውስጥ አወቅ የዜና ምንጮቻችን ሹክ ብለውናል:: በተለይም ለወያኔ አገዛዝ ባለሥልጣናት

- ሥርዓቱ በጨረታና በኪራይ ሰብሳቢነት አገር እያጠፉ መሆኑን ፊት ለፊት ማስጠንቀቁ፣
- የወያኔ ከፍተኛ ባለሥልጣናት በየስብሰባቸው ላይ ሙስናንና ብልሹ አስተዳደርን ለማስተካከል ብናወራም፣ ካዳራሽ ስንወጣ፣ የየራሳችን በዘመድ አዝማድ፣ በብሄር እና በአብሮ አደግነት የተዋቀሩ ኔትዎርኮች ለመከላከል ነው የምንጥረው፣ በዚህም ከተጠያቂነት ለመሸሽ በደላሎች በኩል እናስፈጽማለን ብሎ ላለፉት 25 ዓመታት ጸሀይ የሞቀውን የሥርዓቱን ማንነት በአደባባይ መናገሩ፣

ያስቆጣቸው የወያኔ ቱባ ቱባ ሰዎች የዲስፐሊን እርምጃ ካልተወሰደበት በሚል ጥረት እያደረጉ መሆኑ ታውቋል:: ሰሞኑን የህዝብ ብሶት ለወለደው እና በብዙ የሀገሪቱ ክፍሎች ለፈነዳው የተቃውሞ እንቅስቃሴ ተሳታፊዎችም የልብ ልብ የሰጣቸው ይኸው የኃይለማርያም ንግግር ነው በሚል ክሳቸውን ለማጠናከር እየሞከሩ መሆኑን ምንጮቻችን ገልጸውልናል:: “የወያኔ ሥርዓት የተዋቀረባቸውን ዋና ዋና አላባዊያን (የወያኔ ማንነት መገለጫዎችን) ካልለወጥን ብሎ ኃይለማርያም ያቀረበው ጥሪ ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ካልሆነ በስተቀር ተግባራዊ ሊሆን የማይችል መሆኑንም ግልጽ ነው” ያሉን አንድ ተንታኝ፣ “ለምን?” ስንላቸው ”ጥያቄው መሠረታዊ ለውጥን የሚሻ ነውና“ የሚል መልስ ሰጥተውናል::

ምንጮቻችን የወያኔ አፋኝ ሃይሎች ሰሞኑን የተቀሰቀሰው ህዝባዊ ተቃውሞ በሃይል ይደፈጥጡ ዘንድ መመሪያ መሰጠቱንም አክለው ገልጸውልናል:: በተጨማሪም ከዚህ በፊት በወያኔ መከፋፈል ወቅት የተባረሩትን አመራሮች መልሶ በማስገባት፣ ዘረኛውን አገዛዝ ጠጋግኖ ለማቆየት እና ከአንድ ቋንቋ ተናጋሪዎች የተመዘዙ ጥቂት ሰዎች ከጥቅም ተጋሪዎቻቸው ጋር የያዙትን የበላይነት ዕድሜ ለመቀጠል ጥረት እየተደረገ ነው:: ሰዬ አብርሃን ጨምሮ ከብዙዎቹ የተባረሩት የወያኔ አመራሮች ጋር ምክክር እየተደረገ ሲሆን፣ እስካሁን ድረስ ገብሩ አሥራት እና ዓለም ሰገድ በዚህ የእርቅ ሂደት ስለመካተታቸው ጥርጣሬ እንዳላቸው ምንጮቻችን አሳውቀውናል::